# ሸሸት እና ምሸት

ሄኖክ የሺጥላ

May 31, 2016

አንዳንዴ ከሚሰማህ ፥ እለት እለት የነበስህን ክር በ « ለምን » ጥያቄ ከሚያከረው ሞጋች « እንዴት» የሚሉት ሃሳብ እርፈት ትሻለህ ። አንዳንዴ ዝም ያለ ህይወት ፥ ይናፍቅሃል ። በሰማይ ላይ እንደ ፈላጋቸው ፥ ያለ ክልል ፥ ያለ ቀጠና ፥ ያለ የ ድንበር ላይ ፍተሻ ፥ ያለ ዜግነት የሚበሩት ወፎች ነፃነት ከ ውዱ እና ውዴ ከተባለው የ ሰው ልጅ የተነጠቀበትን እንቆቅልሽ እያሰብክ ፥ ከእንስሶች ሁሉ የተሻለው ሰው ከእንስሶች ሁሉ ነፃነቱንም ያጣው እሱ ራሱ ሰው ስለመሆኑ እያሰብክ ትቆዝማለህ ፥ ትገረማለህ ፥ ዝም ባለ ጬኸት ውስጥ « ይኽ ለምን እና እንዴትስ ሲሆን ሆነ » ብለኽ ትጠይቃለህ ። አይ ሰው !

ያኔ በኤደን ገነት ፥ «አባታችን» አዳም ለእንስሶች የገቢር ስም በሚያወጣበት ዘመን ፥ መርዛማውን እና ተናዳፊው ፍጥረት «እባብ» ፥ ገራሙን እና ሲያርዱት ካራ እየሳሉም ሳር የሚበላውን ሞኛሞኝ ፍጥረት ደሞ « በግ» እያለ ሲጠራ ፥ የሰው ልጅ ከእንስሶቹ ለመሻሉ ፥ የበላይ ስለመሆኑ ስያሜው እና ስም አወጣጡ ፥ የእንስሳቱን ተፈጥሯዊ የባህሪይ ቀመር እና የማንነት ልክ ፥ ምንነት እና ማንነት በስማቸው ገልጦ ማስቀመጥ በመቻሉ ይመስለኛል ።

ዛሬ ያ አዳም ፥ በፍጥረታቶች ላይ አለቃ የነበረው ፥ ያ «የ አምላክ አምሳያ » ፥ ያ በገነት ይመላለስ የነበረው እና ከመላእክቶችም በላይ ሃይል የነበረው የሰው ልጅ ፥ ስም ካወጣላቸው ፥ በቃሉ ካዘዛቸው እንሰሶች አንሶ ፥ የ ወፍ ያህል ነጣነት ሲያጣ ፥ የእርግብ ያህል ሰላም ሲናፍቀው ሲታይ ፥ ምክንያቱን ለመረዳት ፥ እውነቱን ለማስረዳት ፥ ከሚስጥራዊ ውድቀቱ ጀርባ ያለውን እና ፈጠመ የተባለውን ክህደት ልክ ለመረዳት ሃይል ያንስኻል ።

በአንድ ፍሬ በለስ ምክንያት ከማይወጣበት ማጥ ውስጥ የወደቀው አዳም ፥ ትናንት በዘ ፍጥረት ከተሰጠው በላይ ሃይል ፈልጎ ፥ ከሚገዛው በላይ መግዛትን ሽቶ ፥ ከአቅሙ በላይ ወንድነትን ተመኝቶ ፥ ከገነት ተጎትቶ « ጆሮውን ተይዞ» ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ « እንደ ንፍጥ» መሬት ላይ ስለመለጠፉ መጥሃፉም ፥ ወድቀው ታሪካቸውን ከወደቀው አባታቸው የሰሙ ልጆች ፥ ለልጅ ልጆቻቸው ያወሩት ታሪክም ያወራል ።

እኛም የዚያ ደደብ አዳም ልጆች በመሆናችን ፥ ዛሬም ከተሰጠን በላይ የምንሻ ፥ ከያዝነው በላይ ማካበት የማይታክተን ፥ ከገዛነው በላይ መግዛት የምንወድ ፥ ከገደልነው በላይ ለመግደል የምንተጋ ብኩኖች ነን ። የሚገርመው ደሞ አዳም ባልዋጠው ፥ ግሮሮ ላይ ተንጠልጥሎ በቀረ ፥ ባንዲት በለስ ፍሬ ይኽንን ሁሉ ግርማውን ፥ ሞገሱን ፥ በፍጥረታት ላይ ማዘዙን ሲያጣ ፥ እኛም የአባታችን ልጆች ነንና « እሳት አመድ ወልዷልና » ፥ ወደዛኛው አለም ይዘነው በማንሄድው ፥ በማይከተለን ብሎም ነገ ላፈር ምግብ ለሚሆነው ስጋችን ስንል የከመርነው ኩነኔ ፥ ያደረስነው በደል ፥ በንፁሃን ላይ የፈጠምነው ስቃይ ፥ ቀምተን ያስራብነው ህዝብ ፥ ያለ ጥፋቱ ፈርጀን በሴራ በትር የመታነው ብሄር ፥ ያለ ስራው ስራ ፥ ያለ ስሙ ስም ሰጥተን ፥ ለተራ ምድራዊ ምቾት ስንል ፥ የገነቱን ፥ የዘላለሙን ፥ ትልቁን ማንነት የናድን የአዳም እውነተኛ ልጆች ነን !!!

በኛ ደም ውስጥ የሚሽከረከረው ፥ በግብራችን ውስጥ የሚታየው ፥ ህዝቦቹን ለማዳን ከጎሊያድ ጋ ለመፋለም ፥ አሎሎ የያዘው ዳዊት ሳይሆን ፥ ወንድሙን አቤልን የገደለው ቃየል ነው ፥ በኛ ማንነት ውስጥ ጎልቶ የወጣው ክብር የዮሴፍን ጉድጓድ ውስጥ የቀበረው የታላቅ ወንድሞች ቅናት ነው ። በኛ ማንነት ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ስብዕና የወንድሙን ምርቃት ለመቀማት ክንዱን የበግ ጠጉር አልብሶ እኔ ያቆብ አይደለሁም የሚለው ማንነት ነው ።

በመጥሃፍ ቅዱስ ውስጥ ኢትዮጵያዊያኖች ከኩሽ ነገድ እንደሆኑ ይናገራል ። ይኼው ጋሼ ኩሽ የባቢሎንን ግንብ ለመስራት የመጀመሪያውን ንድፈ ሃሳብ ወይም ንድፈ ስይጥና ከዘየዱት ውስጥ የመጀመሪያው እንደሆነ ይነገራል ። ምን

ማለት ነው ፥ በደማችን ውስጥ ቋንቋው የተደበላለቀ ፥ የማይግባባ እና የማይስማማ ህዝብን ተንጠልጥሎ በቀረ ግንብ ስር የመፍጠር ብቃት አለን ማለት ነው ።

ለማንኛውም ከራሴ ሽሽቼ ፥ አንድ የፈረንጆች ሬስቶራንት ውስጥ ቁጭ ብያለሁ ፥ በእጄ ላይ የያዝኩትን መጥሃፍ እያገላበጥኩ ፥ አደጉ ተመነደጉ የሚባሉት ሰዎች እንዴት እንደሚኖሩ በጋት እርቀት ላይ እያስተዋልኩ ፥ ከፊት ለፍቴ የተደቀነውን የቴሌቪዥን መስኮት እያየሁ ቀደም ብዬ እራሴን በጠየቅኩት ጥያቄ ፥ መልስ ለሌለው መልስ ውስጤን እያዋዘሁ ቁጭ ብያለሁ ። በግምት ከምሽቱ ሁለት ሰአት ይሆናል ። በኔ ቤት ፥ እስኪ ከሃገሬ ስቃይ ፥ ወይም የስቃይ ሃሳብ መንፈሴን እረፍት ልስጥና ፥ የተመቻቸው ሰዎች ምቾት ምን እንደሚመስል በጥሞና ለማየት እና ለማስተዋል ፥ ከዚያም በነሱ ምቾት እና በኛ ውርደት መሃከል ያልውን አርበ ሰፊ የ ልዩነት ጎዳና ላጤን ፥ ላብሰለስል ፥ ብሎም ለህዝብ ላሳወቅ በማሰብ ነበር ።

ከፍት ለፊቴ ያለው የቴሌቪዥን መስኮት « በኢትዮጵያ በድርቅ ስለተጎዱ ወገኖች እና አፋጣኝ እርዳታ ስለሚያስፈልጋቸው ምናምን ሚሊዮን ህዝቦች » ያወራል ።

« አየኽ!» አለኝ ውስጤ « አየኽ!» በለሱን ከበላኽ የትም ብትሄድ ሰው መሆንኽ አያበቃም ። እውነት ነው ሽሽት እና ምሽት ይኽንን ይመስላል ። የወራዳ መሪዎች ፥ የለማኝ አስተዳደር ዘመን ልጆች ፥ እኛ!